# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 7 ሰኔ 19 2000 ዓ.ም

## በብራስልስ ዶ/ር ብርሃኑን እንዲቋቋሙ በገንዘብ የተገዙ የባዕድ ደላሎች ተላኩ

የአውሮፓ ፓርላማ ፤የዶክተር ብርሀኑ ነጋን ምስክርነት ለመስማት በተቀመጠበት መድረክ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በዓለማ ዐቀፉ ህብረተሰብ ፊት አሳፋሪ ቅሌትና አስነዋሪ ተግባር መፈፀሙን ሂደቱን በስፍራው ተገኝቶ የተከታተለው ሪፖርተራችን ዘገበ።

ትናንት ረቡዕ እ.ኤ.አ ሰኔ 25 ቀን 2008 ዓ.ም በብራሰልስ-ቤልጅየም በተደረገው የአውሮፓ ፓርላማ ውይይት ላይ፤የመለስ አገዛዝን ወክለው ዶክተር ብርሀኑን እንዲቋቋሙ የተላኩት የኢትዮጵያ መንግስት ዲፕሎማቶች ሳይሆኑ፤በብዙ ሚሊዮን ገንዘብ እየተከፈለው የሚሰራ ዲ.ኤል.ኤ ፓይፐር የተሰኘ የፓለቲካ ደለላ ድርጅት መሆኑ ተሳታፊዎቹን አስደንግጧል።የመለስ አገዛዝ፤ከድሀው ህዝብ ጉሮሮ እየነጠቀ የሚከፍለውና የዲፕሎማሲ ስራ እንዲሰራለት የቀጠረው ዲ.ኤል.ኤ ፓይፐር የተባለው ኩባንያ ተወካይ፤ዶ/ር ብርሀኑ የሁሉንም ቀልብ የሳበ ንግግር ካቀረቡ በሁዋላ ራሳቸውን በማስተዋወቅ ለሚስ አና ጎሜዝ እና ለዶ/ር ብርሀኑ ጥያቄ አቅርበዋል።የኩባንያው ተወካይ ያቀረቡት ጥያቄ” ለምን ወደ ኢትዮጵያ ሄዳችሁ  እንደነ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም አትታገሉም?”የሚል ሲሆን፤ተጠያቂዎቹም ለጥያቄው በቂ መልስ ሰጥተዋል።

ሚስ አና ጎሜዝ በሰጡት ምላሽ ፤በአገራቸው በፖርቱጋል እንደመለስ ዜናዊ ዓይነት አምባገነን ገዥ እንደነበረና እርሱንም ከውስጥና ከውጪ በተደረገ ትግል እንደጣሉት በጠያቂው ማንነት ግራ የተጋቡት የእንግሊዝ የሌበር ፓርቲ ቃል አቀባይና የአፍሪካ፣ካሪቢያንን ፓስፊክ አገሮች ፓርላማ ህብረት ምክትል ፕሬዝዳንት ግሌኒ ኪኖክ በበኩላቸው በኢትዮጵያ እየተባባሰ ስለመጣው የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ በቅርቡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያወጣውን መግለጫ በመደገፍ የአውሮፓ ህብረትን ዝምታ ነቅፈዋል።

ዶ/ር ብርሀኑ ለጠያቂያቸው በሰጡት መልስ ደግሞ” እናንተ ኤች.አር 2003ን ለመግደል ያላደረጋችሁት ጥረት አልነበረም፤የበሰበሰ፣በሙስና የተዘፈቀ እና ወንጀለኛ የሆነን መንግስት እየደገፋችሁ፤ከደሀው ኢትዮጵያዊ ጉሮሮ የሚነጠቀውን ገንዘብ ትወስዳላችሁ።እኛ፤ አገዛዙ ለራሱ በሚጠቅመው መልኩና ባስቀመጠልን ህግና ቀመር አንፋለምም።እንዲህ አድርጉ እያለ በሚያዘን መሰረት ልንታገል አንችልም”ብለዋል።በአጠቃላይ በምላሾቹ ድንጋጤ ላይ የወደቁት የኩባንያው ተወካዮችም በስተመጨረሻ ይቅርታ ጠይቀዋል።

የመለስ አገዛዝ እራሱን በማጋለጥ የውጭ ኩባንያ መላኩ ፣ታማኝ ዲፕሎማት መጥፋቱን ፣በግንቦት 7 ንቅናቄ ስጋት የፈጠረበት መሆኑንና ከዲፕሎማሲያዊ ጨዋታ ውጭ እየሆነ መምጣቱን ያሳያል ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች አመልክተዋል። ዶ/ር ብርሀኑ አያይዘውም “የመለስ አገዛዝ ፣የአገሪቱን ባህላዊ የሽምግልና ስርአት ገድሏል፣ፍርድቤቶችን በአለም ህዝብ ፊት አዋርዷል፣ፓርላማውን እንደፈለገ እንደ አሻንጉሊት ይጫወትበታል ብለዋል።

በመጨረሻም “ሙጋቤን ህገወጥ መሪ ነው፣ ብሎ የፈረጀ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እና ማንኛውንም ዓይነት ማዕቀብ በሙጋቤ ላይ ለመጣል ዝግጁ የሆነ የአውሮፓ ፓርላማ፤ከሙጋቤ ያልተናነሰ አምባገነን ለሆነውና ለንፁህን ዜጎች ጭፍጨፋ ተጠያቂ ለሆነው የመለስ አገዛዝ ፖለቲካዊ ድጋፍ ሊሰጡት አይገባም ብለዋል።ዶ/ር ብርሀኑ ከትናንት በስቲያ ማክሰኞ ከአውሮፓ ህብረት ፓርላማና ከአውሮፓ ኮሚሽን ባለስልጣናት ጋር ውጤታማ ውይይትም አካሂደዋል።

## ረሀቡና እልቂቱ ከፍቷል ህፃናት እንደቅጠል እየረገፉ ነው “ግልፅ መልዕክት ደርሶናል፤ምግብ የለም” የተመድ ባለስልጣን

በኢትዮጵያ የተከሰተውን የረሀብ መጠን ለማረጋገጥ ባለፉት ቀናት ወደ አገሪቱ በመዝለቅ ጉብኝት ሲያደርጉ የከረሙት የተ.መ.ድ የህፃናት ፈንድ ከፍተኛ ባለስልጣን፤በአገሪቱ ዳር እስከ ዳር ህፃናት በምግብ እጦት እየሞቱ እንደሚገኙ አጋለጡ። ረሀቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይበልጥ እየከፋና እየተባባሰ እንደሚሄድም አስጠንቅቀዋል።የመንግስታቱ ድርጅት የህፃናት መርጃ ፈንድ ምክትል ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ሂልድ ጆንሰን ትናንት አዲስ አበባ ውስጥ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በተለየ መልኩ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች ባደረጉት ጉብኝት የረሀቡና የችግሩ መጠን አስደንጋጭና ዘግናኝ ደረጃ ላይ መድረሱን ተረድተዋል።“በሄድንባቸው ቦታዎች ሁሉ ሰዎች በጓዳቸው የሚላስና የሚቀመስ የላቸውም፤እህል መግዣ ሳንቲምም የላቸውም፤በማሳቸው ወይም በቀያቸው የሚታይ ተስፋ ሰጭ ሰብል የለም፤ሰራተኞቻችን ከተሰማሩባቸው ሌሎች በርካታ አካባቢዎችም የሚደርሱን ሪፖርቶች ተመሳሳይ ናቸው”ብለዋል።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል፣

## የኢትዮጵያውያኑ ድጋፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል “ሰላማዊ ትግሉ የመለስ መቀለጃ ሆኗል”

አቶ ቸኮል ጌታሁን

በዶክተር ብርሀኑ ነጋ የሚመራው የግንቦት 7 ለፍትህ፣ለዲሞክራሲና ለነፃነት ንቅናቄ ልዑክ ፤ባለፈው ሳምንት በኔዘርላንድና በጀርመን  የጀመረውን የድርጅቱን ዓላማ የማስተዋወቅ ተግባር አጠናክሮ በመቀጠል፤ በኖርዌይ በስዊድን እና በቤልጅየም ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ከመንግስታት ተወካዮች፣ ከአውሮፓ ህብረት የፓርላማ አባላትና ከህብረቱ ኮሚሽን ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ውጤታማ ውይይት አካሄደ።

የግንቦት 7 ልሳን ሪፖርተሮች ከየስፍራዎቹ እንደዘገቡት፤በየአገራቱ በተደረጉት ስብሰባዎች በርካታ ኢትዮጵየውያን ተገኝተው በንቅናቄው ዙሪያ ከልዑካኑ መሪዎች ጋር ጥልቅ ውይይት አካሂደዋል። ሀሳቦች ያለ አንዳች ገደብ እንዲንሸራሸሩ በተደረገባቸው በእነዚህ ስብሰባዎች ከአንዳንድ ተሳታፊዎች ጠንካራ ጥያቄዎች የተሰነዘሩ ሲሆን፤ተሰብሳቢዎች እርካታቸውን እስኪገልፁ ድረስ በልዑኩ መሪዎች አማካይነት አጥጋቢ ምላሽ ተሰጥቷል።የስቶኮሆልሙን ስብሰባ ከዶክተር ብርሀኑ

..ወደ ገጽ2 ዞሯል፤

# ርእሰ አንቀጽ

## ሃገር እንዳይፈርስ ሁሉም ባለበት ዘብ ይቁም

«ዘ ፈንድ ፎር ፒስ» የተሰኘው የአለም ሠላም ሁኔታ ዘጋቢ ድርጅት አራተኛውን «ፌይልድ ስቴትስ ኢንዴክስ» (የውዳቂ ሃገሮች መመዘኛ) ዘገባውን ሰሞኑን አውጥቶአል:: በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት 177 ሃገሮች ሠላማቸው ተናግቶ ለመውደቅ አደጋ ከጋጠማቸው ሃገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ በ18ኛ ደረጃ እንደምትገኝ አስታውቋል :: የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃውን የያዙት ሱዳንና ዚምባቡዌ ሲሆኑ ፤ ኤርትራ 44ኛ ኖርዌይ 177ኛ ሆነዋል ::

ሃገሮቹ የተመዘኑት በ12 መለኪያዎች ሲሆን የሰብአዊ መብት ጥሰት፤ እርስ በርስ የተከፋፈሉ ልሂቃን መኖር (ፋክሽናላይዝድ ኤሊትስ)፤ በዜጎች ሃገር ጥሎ መሰደድ ፤ የሥርአቱ ተአማኒ ያለመሆን፤ እንዲሁም ያልተመጣጠነ ዕድገት (ገቢ) ከመለኪያዎቹ መሃል ነበሩ:: የመለስ አገዛዝ የተንሰራፋባት ኢትዮጵያ በነዚህ መለኪያዎች ሁሉ አሳፋሪ ደረጃ አግኝታለች:: የመጨረሻው መጥፎ ነጥብ 10 ከ 10 በሆነበት መለኪያ ላይ የመለስ አገዛዝ በዜጎች ሃገር ጥሎ መሰደድ 7.5፤ ባልተመጣጠነ እድገት (ገቢ) 8.5፤ በኢኮኖሚ ድቀት 8.0፤ በሰብአዊ መብት ጥሰት 8.0፤ እርስ በርስ በተከፋፈሉ ልሂቃን 8.7 በማግኘት የመጥፎ ሃገሮች አውራ ለመሆን በቅቶአል:: በትምህርት ፖሊሲው የሚመፃደቀው አገዛዝ፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በአለም ላይ እጅግ ዝቅተኛ ከሆኑት አንዱ በመሆን የተማሪዎቹ ብዛት 18 በመቶ መሆኑንም ዘገባው አሳይቶአል:: በኢኮኖሚ ገቢ አለመመጣጠንም አስከፊ ደረጃ ያስመዘገበው የመለስ አገዛዝ፤ ከጠቅላላው ህዝብ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኘው 10 በመቶ ዜጋ ከሃገሪቱ ሃብት ሲሶውን (33.7 ፐርሰንት) እንደሚቆጣጠርና ይህም ለሃገሪቱ አለመረጋጋት ምክንያት እንደሚሆን አስረግጦአል ::

አሃዞቹ ግልፅ ናቸው:: በመሬት ላይ ያለውን የህዝባችንን ሰቆቃ ነው የሚያንፀባርቁት :: ችግሩ ይህንን አሃዝ የሚያዩትና ጥናቱንም የሚያስደርጉት ምዕራባውያን ናቸው ይህንኑ አስከፊ ሥርአት በትከሻችን ላይ የጎለቱብን:: የጦር መኮንኖቹን የሚያሰለጥኑ፤ የምንገደልበትን ጥይት የሚያቀብሉት እነርሱው ናቸው :: ግንቦት7 ይህ የምዕራባውያን ድጎማና ድጋፍ እንዲቆም በውጪ ሃገር የሚገኙ ዜጎቻችንን የማስተባበር ሰፊ መርሃ ግብር ዘርግቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: በአውሮፓ ፓርላማዎችና መንግስታት ዘንድ ንቅናቄአችን ያገኘው አቀባበል ተስፋ የሚሰጥ ነው :: የኢትዮጵያውያኑም ድጋፍ ለትግል የሚያተባ :: ይሄው ጅማሮ በቀጣዩ ሳምንት ወደ አሜሪከ በማቅናት ዋሽንግተን ዲሲ ላይ በሚጀምር ህዝባዊ ስብሰባ ይቀደሳል:: ውጤቱም ከአውሮፓው ሊልቅ እንጂ ያንሳል ብለን አንገምትም ::

በውጪ ስምሪት «ግንቦት 7» ሲያስገመግም፤ በሃገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎች ከአገዛዝ ሥርአቱ ጋር የሚያደርጉት ትንንቅ ቀጥሎአል:: እንዳቅማቸውም ቢሆን ከአስቸጋሪ ሁኔታ ጋር በመጋፈጥ የገቡበት ትንቅንቅ ስርአቱን ፋታ በመንሳት ምን ያህል ከህዝብ መብትና ነጻነት ጋር ግብ ግብ መግጠሙን ለመመስከር በአርአያነት የሚጫወቱት ሚና ትልቅ ነው። ሌላውንም የመለስ የግፍ አገዛዝ ይብቃ የሚለውን ድርጅትና ግለሰብ ወደ መድረኩ ጋብዘዋል:: እነዚህ ሁሉ ጅረቶች በጋራ የሚፈጥሩት ማአበል ነው ከሃዲውን ሥርአት አንድም ወደ ምክክር ማዕድ እምቢተኛም ከሆነ እንዲወገድ የሚያስገድደው ብለን አናምናለን ::

ለመውደቅ አደጋ ላይ ከሚገኙ ሃገሮች በ18ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጦ፤ አመራሬ ድንቅ ፤ ዕድገት ተኮር መንግስት ነኝ ብሎ ራሱን ማሞከሸት እንኩዋን አቅቶት ፤ «የተራበው 6 ሚሊዮን ሳይሆን 3 ሚሊዮን ብቻ ነው»፤ «ለሱዳን መሬት ለመስጠት ተስማማሁ አንጂ ገና ችከል ስላልቸከልኩ በከሃዲነት አትክሰሱኝ» ብሎ መከራከር መጀመሩ፤ ውድቀቱ ለራሱም እየገባው ለመሆኑ ምልክት ነውና፤ ከመሠረታዊ የዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎቻችን ሳንዘናጋ፤ በህዝቡ መብትና በሃገራችን ዘላቂ ጥቅም ላይ በጋራ እንቁም በማለት የ«ግንቦት ሰባት ንቅናቄ» ህዝባዊ ጥሪውን ያስተላልፋል:: ወደ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚወስዱንን መንገዶች መጥረግ ላይ በሃሳብ እንዳንከፋፈልና፤ በመከላከያና የፀጥታ ሃይሉ ከገዢው ፓርቲ መለየት፤ የሚዲያና ምርጫ ቦርድ ከገዢው ፓርቲ መነጠል፤ መሠረተዊ ጉዳዮች ላይ በየዋህነት እንዳንለያይ፣ ህዝብን የስልጣን ባለቤት፣ መለስን የሃገራችን የመጨረሻው አምባገነን በሚያደርገው ጉዳይ ላይ የአመለካከት አንድነት እንዲኖረን ንቅናቄያችን አበክሮ ይሚገተል ::

## ረሀቡና እልቂቱ ከፍቷል ከገጽ 1የዞረ

ዳይሬክተሯ አክለውም፡-”ከሂድንባቸው አካባቢዎች ሁሉ ግልፅ መልዕክት ደርሶናል፤ምግብ የለም” ሲሉ ኢትዮጵያውያን በሞት ድባብ ስር እንደሚገኙ እቅጩን ተናግረዋል።

ዜጎች በረሀብ እያለቁ በሚገኙበት ሁኔታ የረሀብተኞችን ቀጥር በመቀነስና እልቂቱን በመደበቅ ስራ ላይ ተጠምዶ ለከረመው ለአቶ መለስ አገዛዝ የዳይሬክተሯ መግለጫ ጆሮ ጭው የሚያደርግ መሆኑን ታዛቢዎች ይናገራሉ።

የመለስ አገዛዝ ረሀብና እልቂትን ፈፅሞ መደበቅ እንደማይቻል ከሀይለስላሴ ስርዓትና ከደርግ መንግስት አለመማሩ በእጅጉ ይገርማል የሚሉት እኝሁ ታዛቢዎች፤በሁሉም መስኮች ታሪክ ራሱን ሲደግም እያየን ነው ብለዋል።

አንድ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የመንግስት ባለስልጣን ለግንቦት 7 በሰጡት አስተያየትም የ1966 ዓ.ም ድርቅ ሊባባስ የቻለው ዓፄ ሀይለስላሴ በጊዜው የሚያከብሩት 80ኛ ዓመት የልደት በዓላቸው ድምቀቱ እንዳይደበዝዝ ረሀቡን በመደበቃቸው፤የ1977 ዓ.ም ረሀብ ሊባባስ የቻለው ደርግ በጊዜው ሊያከብር የተዘጋጀው የኢሰፓ ምስረታ በዓል ድምቀት እንዳይደበዝዝ ችግሩን በመሸሸጉ እንደሆነ፤አሁንም እልቂቱ እየከፋ የመጣው “በፖለቲካዊ ጭቃ ያደፈውና የጨቀየው የ’ሚሊኒየም’ በዓል” ድምቀት እንዳይበላሽ ተብሎ ረሀቡ እንዲደበቅ በመደረጉ እንደሆነ ተናግረዋል።

በ1977 ድርቅ ደርግ ለኢሰፓ ምስረታና ለ10ኛው አብዮት በዓል በአስርት ሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር ማፍሰሱ የሚታወስ ሲሆን፤የአቶ መለስ አገዛዝ ደግሞ ህዝብ እየረገፈ ባለበት በአሁኑ ጊዜ “በፖለቲካ ለጨቀየው ሚሊኒየም” ወደ 400 ሚሊኒየም ማውጣቱ ይነገራል።እንዲሁም በዚህ የሚበላ በጠፋበት ጊዜ ለጦርነት ሲል የመከላከያ በጀቱን መጨመሩ በዓለማቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ ትችት ሲያስከትል፤የትጥቅ ትግል የመረጡ ተቃዋሚዎች በበኩላቸው “የጦር መሳሪያ ብዛት ህዝባዊ ትግልን ሊያቆም ወይም ሊገታ አይችልም” ይላሉ።

## የኢትዮጵያውያኑ ድጋፍ ከገጽ 1የዞረ

ጋር በመሆን የመሩት የንቅናቄው መስራች አባል አቶ ቸኮል ጌታሁን ፤የግንቦት 7ን መመስረት አንገብጋቢነት ባሰረዱበት የመክፈቻ ንግግራቸው ”ሰላማዊ ትግል በመለስ አገዛዝ አቢዩዝ ሆኗል” ሲሉ ገለልጸዋል።

ኢትዮጵያውያኑ በበኩላቸው ግንቦት 7 የኢትዮጵያን ህዝብ ጥያቄ ለመመለስ የነደፋቸው የትግል መስመሮች ተገቢ እንደሆኑና ከዚህ የተሻለ አማራጭ እነደሌለ ግንዛቤ ማግኘታቸውን በመግለፅ፤ከንቅናቄው ጎን ሆነው የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ
የቀድሞ የአዲስ ዜና እና የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ መሰፍን አማን፣አቶ ቸኮል ጌታሁን፣ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ፡፡

# ለነጻነት የሚደረግ ጉዞ

ከ430 ዓመታት የግብፅ ባርነት በኋላ በሙሴ አማካይነት ነፃ የወጡት እስራኤላውያን ፤ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚያደርጉት ጉዞ እጅግ ከባድ፣አስቸጋሪና እልህ አስጨራሽ ነበር።በተለይ በቃዴስ በረሀ ለአርባ ዓመታት ሲጓዙ የአሸዋው ግለት ውስጥ እግራቸውን ከማቃጠል አልፎ እንደቦት ጫማ እስከ ባታቸው ድረስ አስጥሞ ይለበልባቸው ነበር።” ሆኖም…”ይላል ፀሀፊው “…ሆኖም፤ የደስታ መንፈስ አዕምሮአቸውን ሰንጥቆ በልባቸው ይፈስ ነበር።” በመንገዳቸው ላይ መከራና ችግር ተጋርጦ ሳለ፤እንዴት በልባቸው ሀሴት ይፈሳል? ብሎ የሚጠይቅ ካለ መልሱ ቀላልና ግልፅ ነው_ጉዞው የነፃነት ስለሆነ የሚል። አዕምሮአቸውና ልባቸው ከፈርዖን ቀንበር ነፃ መሆኑን ስለተቀበለ የሚል።
አዎ! አካላዊ ነፃነቱ ይህን ተከትሎ የሚመጣ ነው።

“ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለዲሞክራሲና ለነፃነት ንቅናቄ”፤አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ነፃነቱን አውጇዋል ብሎ ያምናል።ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ የመለስን አገዛዝ “አልፈልግህም” በማለት ራሱን ከዳግማዊ ፈርዖን አገዛዝ ነፃ አውጥቱዋል ብሎ ይረዳል።አዎ! ህዝባችን ከሁለት ዓመት በፊት በተከናወነው ሰላማዊ ፍልሚያ ፍላጎቱን፣ምርጫውንና አቋሙን በማሳየት የነፃነት ድሉን ራሱ አውጇል።ሌላው ቀርቶ በኮሮጆ ግልበጣና በካርድ ስርቆት የምርጫውን ውጤት መቀልበስ ያልቻሉት አቶ መለስ፤ “የተጨማሪ 5 ዓመትት ብቻ” የስልጣን ጥያቄ ፤በተማፅኖ መልክ ሲያቀርቡ፤ ለ አቶ መለስ አገዛዝ የ 5 ደቂቃም ዕድሜ ለመፍቀድ እንደማይፈልግ እቅጩን ተናግሩዋል-የኢትዮጵያ ህዝብ።

ሆኖም፤…ሆኖም…አገዛዙ የጨዋታውን ህግ በመጣስና የኢትዮጵያ ህዝብ የተቀዳጀውን ነፃነት በጠመንጃ ለመቀልበስ በመወሰን፤ በ አገርና በህዝብ ላይ መጠነ -ሰፊ ጥፋት ፈፅሟል፤እየፈፀመም ይገኛል።ይህ ለሁላችንም ግልፅ ስለሆነ ወደ ዝርዝሩ አልገባም።በአጭሩ ነፃነቱን ያወጀው የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ “በቃዴስ በረሀ” ላይ ይገኛል-በግብፅ እና በከነዓን መካከል ማለት ነው።እንግዲህ “ግንቦት 7” የተመሰረተው፤ በዋነኝነት አዕምሯዊ ነፃነቱን ላወጀው ለኢትዮጵያ ህዝብ አካላዊ ነፃነቱን ለማረጋገጥ ነው።በሌላ አገላለፅ “በአካላዊ ነፃነት ጥማት በረሀ” ላይ ያለውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ወደ ከነዓን /ወደ ነፃነቱ ዳርቻ/ ለማድረስ ነው።
ይህን ስንል፤ከፈርዖናዊ የጭቆና ቀንበር አካልን ለማላቀቅ የሚደረግ ትግል ቀላል እንደማይሆን ይገባናል።የትግሉ ሜዳ እሾህና ኩርንችት ሊበዛበት ይችላል።ይህ ብቻ አይደለም-ግንቦት 7ን ከተቀላቀሉት እጅግ ብዙዎቹ ”በሰላም” ምቾት ያለው ኑሮ የሚኖሩ ከመሆናቸው አንፃር ”እንዴት ይህን መረጡ?” የሚል ጥያቄም ሲነሳ ሰምተናል።መልሳችን ግልፅና አጭር ነው_”ከባርነት መንፈስ ጋር ወይንና ጮማ ከማወራረድ ይልቅ ከወገኖቻችን ጋር በቃዴስ በረሀ መታገልን መረጥን” የሚል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በ”ስመ-ዲሞክራሲ” በጠመንጃ ሲጠመቅ 18 ዓመት ሆነው።ምሁሩ ከዩኒቨርሲቲ ሲባረር፣ሰራተኛው ከስራ ሲቀነስ፣ነጋዴው ሱቁ ሲታሸግ፣ተማሪው በጠመንጃ ሲጠበስ፣ካህን ከቤተ-መቅደስ ፤ሸኪ ከመስጅድ እየታደነ ሲለቀም፣ጋዜጠኛ ከርቸሌ ሲወረወር፣መምህራን፣የታክሲ ባለንብረቶች፣ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ፣ትምህርት ቤቶች፣ሆስፒታሎች…እንደታመሱ፤ወላጆች እንዳለቀሱ፤… ህዝቦች በጅምላ ጥገኛ፣ትምክህተኛ፣ጠባብ ተብለው እንደተወቀሱ …ተቃዋሚዎች እንደተማረሩ፣የአገር አድባሮች እንደተደፈሩ ፤ዳር ድንበሮች በየአቅጣጫው እንደተሸረሸሩ፤ህፃናት በረሀብ እንዳረሩ…እነሆ ሁለት አስር ሊሆነን ነው።በእርግጥም የመለስ አገዛዝ ያልተጣላው የህብረተሰባችን ክፍል የቱ ነው? ?ራሳችንን እንሸንግል ካላልን በስተቀር ሁላችንም ተንቀናል፤ተሰድበናል፤ተዋርደናል፤ጠመንጃው የሳተንም ብንሆን በቁማችን ተገድለናል። ይህን እያዩና እየሰሙ በዝምታ መቀመጥ፤ለአረመኔያዊው አገዛዝ “የአገር ግደል ! ሊቸንሳ “እንደመስጠት ነው።

አሁንም ዕድሜ ለአቶመለስ፤ ለዘመናት ታፍሮና ተከብሮ የኖረው ዳር ድንበራችን የባለጌ መጫዎቻና የእሪያ መራገጫ ሆኗል።ዓፄ ዮሀንስ ”እንኩዋን ለስንዝር መሬቷ ለእፍኝ አፈሯም ስሱ ነን” የማለታቸውን ያህል፤ዓፄ መለስ መሬት ለጠየቃቸው ሁሉ የኢትዮጵያ ግዛት የአዜብ አምባሻ ይመስል ፤ ሽህ ጋሻ እየቆረሱ መስጠታቸው፤ሰውየው የዮሀንስ አብራክ ሳይሆኑ፤የባንዳ ቅሪት መሆናቸውን ነው የሚያመላክተን።አገራዊ ፍቅር የሌለው ብቻ ሳይሆን የአገርን ክቡርነት የማያውቅ ባንዳ ደግሞ የምኒልክ ወንበር ላይ ተቀምጦ እንዲሰነብት አየፈቀድለትም።አገዛዙ ሰፊ ጊዜና ዕድል ተሰጥጦታል፤በሁሉም ዘርፍ ተፈትኖ ወድቋል።

መላው የአገራችን ህዝብ ሆይ!!! ቀበቶህን አጥብቅ!ተነስ! ታጠቅ!!ከግንቦት 7 የፍትህ፣የሰላምና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጎን በመቆም የቃዴስ በረሀን የነፃነት ዳርቻ ጉዞ ተቀላቀል።አባጣ ጎባጣ ቢበዛውም እንኳ፤ጉዞው የነፃነት ስለሆነ የሀሴት መንፈስ በአዕምሮህ አልፎ ወደ ልብህ ይዘልቃል።ጀግናውና ክቡሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!!! ራስህን፣ልጆችህን እና አገርህን ለማዳን ለሚቀርብልህ የትግል ጥሪ በምትችለው አቅም ድጋፍህን ታደርግ ዘንድ ንቅናቄያችን ከወዲሁ ጥሪውን ያቀርብልሀል።ድሉ፤በአጭር ጊዜ ውስጥ የአንተው እንደሆነ ከወዲሁ እናረጋግጥልሀለን።

## ታላቅ የህዝባዊ ስብሰባ ጥሪ
## ከግንቦት 7 የፍትህ፣የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

የግንቦት 7 አመራር አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ የንቅናቄውን አላማና ፕሮግራም ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፣በወቅታዊና አንገብጋቢ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይም ማብራሪያ ይሰጣሉ።

ቀን፡ ቅዳሜ ፡ ጁላይ 5 ቀን 2008፡ሰዐት፡12፡30-3፡30 PM.

የእለቱ እንግዶች ፡ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ
አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ
ዶ/ር ግደይ አሰፋ
አቶ ኤፍሬም ማዴቦና ሌሎችም

በዚህ ወሳኝ መድረክ ተገኝተው በፖለቲካ ትግሉና የሃገራችንን ህልውና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ በአክብሮት ተጋብዘዋል።

ቦታ ፡Merriott Hotel ፣1221 22nd Street,NW, Washington DC 20037. — መግቢያ 30$

# እንዴት እንነሳ

ጽናት ፍቅሩ

በግንቦት 7 ኒውስ ሌተር ላይ ፣ "አገር ይፈርሳል እኛ ተኝተናል" በሚል የቀረበውን ጽሁፍ ተመልክቼዋለሁ።ጸሀፊው ባነሷቸው ነጥቦች ላይ ተንተርሼ የራሴን የመፍትሄ ሀሳብ ላቅርብ።አንዳንዶች፣ የኢትዮጵያ ህልውና ፈተና ውስጥ እየገባ መምጣቱን ደጋግመው ይናገራሉ ።ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም እንደሚሉት "ኢትዮጵያ የተአምር አገር ናት" ካልተባለ በስተቀር አሁን እየታዩ ያሉ ኩነቶች የአገሪቱን ህልውና አደጋ ውስጥ እየጣሉት መምጣታቸውን ማየት የምንችል ይመስለኛል። አምባሳደር ዴቪድ ሺን፣ ከ14 አመት በፊት በጻፉት አንድ ጽሁፍ ላይ ስለዛሬዋ ኢትዮጵያ ይህንን ብለው ነበር " ኢህአዴግ የሚያራምደው ፍልስፍና በአዲሱ ትውልድ ዘንድ ተቀባይነትን ስለማያገኝ፣ ከ4 ምርጫዎች በሁዋላ(20 አመት)፣ገዢው ፓርቲ በስልጣን ለመቆየት ትልቅ ፈተና ውስጥ ይገባል። ስልጣንን ለማቆየት በሚደረግ ትግልም የአገሪቱ ህልውና አደጋ ውስጥ ይወድቃል"።በግጭቶች ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ ምሁራን እንደሚናገሩትም፣ በጠንካራ ሀይል ላይ የሚገኝ ገገር፣የሀይል ሚዛኑ እየከዳው ሲመጣ፣ስልጣኑን ለማቆየት፣ከተቀናቃኞቹ ጋር እልህ አስጨራሽ ግጭት ውስጥ ይገባል።አምባገነኖች፣ጨካኝና ጥልኛ የሚሆኑት በስልጣን ላይ ለመቄየት ጉልበትና እውቀት እያነሳቸው ሲመጣ ነው።

ኢህአዴግ ይዞት የመጣው ና የሚያራምደው "ፍልስፍና" በአዲሱ ትውልድ ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱ በግንቦቱ 1997ቱ ምርጫ የታየ ነገር ነው። ለምሳሌ፣አርሶአደሩን ማእከል ያደረገ ነው የተባለው ልዩ የግብርና ፖሊሲ፣ ከ 17 አመት ሙከራ በሁዋላ ድምር ውጤቱ 8 ሚሊዮን ረሀብተኞችን ማፍራት ና የግብርና ምርቶችን ዋጋ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መጠን ማናር ነው።ለብሄረሰቦችና ግለሰቦች ዲሞክራሲያዊ መብትን ያጎናጽፋል የተባለው ህገመንግስት፣ለተወሰኑ ሰዎች የፈላጭ ቆራጭ መብት ከመስጠት ያለፈ ግልጋሎት አልሰጠም።ህገ መንግስቱ በጆርጅ ኦርዌል ቋንቋ "ሁሉንም በወረቀት እኩል ያደረገ፣በተግባር ግን የተወሰኑ መለሶችን ከሌላው በተሻለ እኩልነትን የሰጠ ነው"። የእነመለስ ቡድን በአስተዳደር መበላሸት ምክንያት ስልጣን ከእጃቸው እየወጣ መምጣቱን ሲያዩ ሁለት መፍትሄዎችን ይወስዳሉ- ህዝቡን በውሸት ለመያዝ በመሞከርና ስልጣን የሚቀናቀናቸውን አሳዶ በመምታት ።ለህዝቡ በየምሽቱ የሚነገረው ፣ ምርት መትረፍረፉን ና አገሪቱ ጥጋብ በጥጋብ መሆኑዋን ነው።በዚያ ምሽት ይህን ዜና የሚሰማው ዜጋ ቀኑን ሙሉ የረባ ነገር ሳይበላ መዋሉን ያውቀዋል።ልጆቹን አብልቶ ማስተማርና ለወግ ለማእረግ ማብቃት ላልቻለው ህዝብ የሚነገረው፣ የተለመደው ፣ኢኮኖሚው በ10 በመቶ አደገ የሚለው ዜና ነው።በክልሎች እና በጎረቤት አገሮች ግጭቶች ሲከሰቱ መልሳቸው፣ "ተቃዋሚዎችና ሻእቢያ ፈጠሩብን " የሚል ነው ።ውሸት ካለዋጣ ሌላው መፍትሄ ተቃዋሚዎችንና ተቺዎችን እያሳደዱ መመታት ነው። በዚህ ስልት በተለይ ከግንቦት 97 በሁዋላ ብዙዎቹ የእነመለስ ጭዳ ሆነዋል።የቆሰለ አውሬ እስኪ ሞት ጠላቶቹን ለመግደል ወደ ሁዋ እንደማይል ሁሉ፣እነመለስም ከግንቦቱ ቁሰለት በሁዋላ፣ከሚፈሩት ሀይል ጋር ሁሉ እየተናከሱ ናቸው።በውጭና በውስጥ የሚያደርጉት ንክሻ ነው እንግዲህ የአገሪቱን ህልውና አደጋ ውስጥ እየጣለው የመጣ።ታዲያ አገር የማዳኛው መፍትሄ ምንድን ነው?ብዙ ጓደኞቼ መፍትሄ ያለው በኢትዮጵያ ህዝብ እጅ ነው ይላሉ።እኔም እስማማለሁ።ታዲያ የኢትዮጵያ ህዝብ ለምን አይነሳም?ለመብቱ፣ለኑሮውና ላገሩ መነሳት እንዳለበት ባለማወቁ ነው ወይስ አሁን ያለው አገዛዝ ተመችቶት? ህዝቡ በአገዛዙ መማረሩን በግንቦት 7፣1997 ምርጫ ወቅት አሳይቷል።ከምርጫው በሁዋላ በተደረገ ጥናትም የእነመለስ የህዝብ ድጋፍ 17 በመቶ ብቻ ነው ።ከመንግስትነት ወርዶ የሰፈር ገዢ ሆኗል ማለት ነው።ታዲያ ለምን አይነሳም? የራሴን ግምቶች ላቅርብ።

ለእይታ እንዲመቸኝ ህዝቡን ለ2 ልክፈለው።በመንግስት ቀጥተኛ ተጽኖ ስር ያለውና በቀጥታ ተጽኖ ስር የሌለው በሚል።የመጀመሪያው ምድብ የቢሮ ሰራተኞችን፣ወታደሩን፣ፖሊሱን፣ተማሪውን፣አስተማሪውን በአጭሩ ደሞዝተኛውን ያጠቃልላል።በዚህ ምድብ የሚገኙ ሰዎች በይፋ መንግስትን ለመቃወም እንዳይችሉ በደህንነት ሀይሎች ክትትል ይደረግባቸዋል።ለወታደሩ፣ለመምህሩ፣ለተማሪው ወዘተ ሰላዮች ተመድበው 24 ሰአት ምን እንደበሉና እንደጠጡ ሳይቀር ይሰልላሉ። ሰራተኞች እድገት ለማግኘት የኢህአዴግ ደጋፊ መሆን አለባቸው።ትልቅ የሰብአዊ መብት ጥሰት ቢሆንም ኢህአዴግ የሚገባው አይደለም።ተማሪዎችም ስለአገራቸው እንዳይወያዩ ፣ሁለት ሶስት ሆነው መቆም እና ማውራት እንኳን አይፈቀድላቸውም።ይህም አልበቃ ብሎ በተለይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን በኢህአዴግ ተማሪዎች በመሙላት ተቃውሞዎች እንዳይነሱ እያደረገ ነው።በዚህ ሁኔታ ውስጥ አንድ አምሳል አንድ አካል ሆኖ መነሳት ከባድ ነው።ማን ማንን ያምነዋልና?

ከመንግስት ቀጥተኛ ተጽኖ ውጭ ያለው ሁለተኛው ክፍል ደግሞ፣ በተለይ ገበሬው፣ ንቃቱ ከሚፈጥርበት ችግር በተጨማሪ ተቃውሞ እንኳ ቢያነሳ ከመሬቱ ከመፈናቀል አንስቶ ለእስርና ድብደባ ይዳረጋል ።ነጋዴውም ቢሆን ከኢህአዴግ የንግድ ተቋማት የተረፈውን ለማግኘት አንገቱን መድፋት እንደሚያዋጣው ያውቃል።

በአጠቃላይ ምክንያቶቹ ሁሉ በሁለት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ያጠነጥናሉ-ቡኑሮና በደህንነት ዙሪያ።እነዚህ ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ህዝቡ በገዢዎች ላይ እንዳይነሳ አድርገውታል።ምናልባት የፈረንሳይ አብዮት ታሪክ ይቀራረብ ይሆናል።በድህነት የሚኖርና የሚበላውን ያጣ ህዝብ፣ሌት ተቀን የሚያስበው፣ያስራበውን ሀይል ማባረር ሳይሆን ተለማምጦም ቢሆን ዳቦ ማግኘት ነው።ትግል ለመታገል ሆድ መሙላት አለበት።የእውቁ የስነልቦና ሊቅ የማስሎው ንድፈ ሃሳብ የሚነግረንም፣ የመብትና የፖለቲካ ጥያቄዎችን ለማንሳት በመጀመሪያ ሆድ በደንብ መሙላት አለበት ።

በደህንነት ዙሪያ ያለውን ችግር ለማየት ከግንቦት 7፣1997 ምርጫ በሁዋላ የተፈጠረውን ክስተት ማየቱ በቂ ነው።በርካታ የቅንጅት ደጋፊ ወጣቶች በደህንነት ሀይሎች እየተለቀሙ ተገድለዋል፣ ታስረዋል፣ ተሰደዋል።ይህ እርምጃም የ "እኔን ያየህ ተቀጣ ስሜት እንዲፈጠር አድርጓል።ፍራንሲስ ካፍካ ይመስለኛል፣የአፍሪካ መሪዎች 2/3ኛ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ስልጣናቸውን ለማቆየት የደህንነት ስራ ሲሰሩ ነው ያለው።በርግጥም የመለስ መንግስት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያጠፋው ህዝቡን ለመቆጣጠር የደህንነት ስራ ሲሰራ ነው።

እነዚህ ምክንያቶች ህዝቡ በመሪው ላይ ፈጥኖ እንዳይነሳ የሚያደርጉ ቢሆንም ፍጹም ናቸው ማለት አይደለም። ፈጽሞ ተስፋ የሚስቆርጡም አይደሉም።እነዚህን ምክንያቶች ግምት ውስጥ የሚያስገባ ስትራቴጂ ከተነደፈ ህዝቡን ማስነሳት ፣ማታገልና ውጤት ማምጣት ይቻላል።የግንቦት 7 ንቅናቄ፣በደህንነት ምክንያት የሚፈጠረውን ችግር ተገንዝቦ፣በህቡ መደራጀትን እንደ አማራጭ የትግል ስልት መውሰዱ፣ ከግንቦቱ ምርጫ በሁዋላ ከተፈጠረው ኩነት መማሩን ያሳያል።በእኔ እምነት ትክክለኛ ስልት ነው።ሌላው መመለስ ያለበት ጥያቄ ከኑሮ ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን ደንቃራ እንዴት መመለስ ይቻላል የሚለው ነው።በእኔ እምነት ይህም ከባድ ጥያቄ አይመስለኝም።የተወሰኑ ሰዎችን በመምረጥ ትግሉን እንዲያቀጣጥሉ ማድረግ ነው።የእነዚህን ሰዎች ኑሮም ለመደጎም ጥረት ማድረግ ነው።በእግር ኳስ ጫዋታ እውነተኛ ተጫዋቾቹ 11ዱ ናቸው እንጅ ደጋፊዎች አይደሉም።11ዱ ናቸው ደጋፊዎችን የሚስቡት፣ጫዎታ ተጫውተው ቡድኑን ከውድቀት የሚያድኑት።